# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ
## ፬(4)ኛ ክፍል


የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተስማማ



አስማምቶ አዘጋጆች

ትዘዘው አድጎ ደስታ

አልሃምዱ አብዶ አህመድ

የጥራት ክትትል

ፍሬህይወት አሠፋ ከበደ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለምዓቀፍ የልማት ድርጅት /United States Agency for International Development (USAID)/ በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮና በREAD TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም /General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II /ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው።

ISBN: 978-99944-2-363-7

# ማውጫ

ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች ............ v

1ኛ ሳምንት ............ 1

2ኛ ሳምንት ............ 6

3ኛ ሳምንት ............ 10

4ኛ ሳምንት ............ 14

5ኛ ሳምንት ............ 19

6ኛ ሳምንት ............ 24

7ኛ ሳምንት ............ 28

8ኛ ሳምንት ............ 33

9ኛ ሳምንት ............ 37

10ኛ ሳምንት ............ 41

11ኛ ሳምንት ............ 45

12ኛ ሳምንት ............ 50

13ኛ ሳምንት ............ 54

14ኛ ሳምንት ............ 60

15ኛ ሳምንት ............ 65

16ኛ ሳምንት ........ 69
17ኛ ሳምንት ........ 73
18ኛ ሳምንት ........ 77
19ኛ ሳምንት ........ 81
20ኛ ሳምንት ........ 85
21ኛ ሳምንት ........ 89
22ኛ ሳምንት ........ 94
23ኛ ሳምንት ........ 99
24ኛ ሳምንት ........ 104
25ኛ ሳምንት ........ 108
26ኛ ሳምንት ........ 113
27ኛ ሳምንት ........ 118
28ኛ ሳምንት ........ 122
29ኛ ሳምንት ........ 126
30ኛ ሳምንት ........ 130

# ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሕጻናትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የማዳመጥና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማበልፀግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃትምህርት አካል ነው:: መጽሐፉም ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ሕጻናት ማንበብና መጻፍ እንዴት እንደሚማሩ የተደረገ ጥናቶችንና የአማርኛ ቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት ነው::

የዚህ የአፍመፍቻ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት እና መርሃትምህርት የተወሰኑ መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው::

1. ሕጻናት እንግዳ ቃላትን ለማንበብና ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር ለመጻፍ፣ የቋንቋው ፊደላት የሚወክሏቸውን ድምፃች መማር ይጠበቅባቸዋል፤ ይህ ትምህርት የ1ኛና የ2ኛ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርትና መርሃትምህርት አካል ነው::

2. ሕጻናት በተቻለ መጠን ቃላትን ቀጥሎም ዓረፍተነገሮችን ማንበብ አለባቸው፤ እነዚህ ቃላትና ዓረፍተነገሮች በተማሯቸው ፊደላት የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፤
3. ሕጻናት በፍጥነት፣ በትክክልና ያለችግር እንዲያነቡና ራሳቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በትክክልና በግልጽ ቋንቋ ለመግለጽ እንዲችሉ የማንበብ፣ የመናገርና የመጻፍ በርካታ ተከታታይ ልምምዶች ማድረግ አለባቸው፤

4. ሕጻናት አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የቃላቱንም ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያነቡትን ይረዳሉ፤ ቋንቋቸውንም በንግግርና በጽሑፍ በአግባቡ ይጠቀሙበታል፤

5. ሕጻናቱ ተረቶችን/ታሪኮችንና ሌሎች ጽሑፎችን አንብበው ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ማዳበር አለባቸው::

## ልጅዎን በቤት ውስጥ ይርዱ!

ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብና መጻፍ እንዲማሩና ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ በቤት ውስጥ መርዳት ከሚችሉባቸው አጠቃላይ መንገዶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

1. ለልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን ይንገሯቸው::

2. ልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን እንዲናገሩ፣ ሁነቶችን መልሰው እንዲተርኩና ዜናዎችን እንዲለዋወጡ ይጠይቋቸው::

3. ልጆችዎን እርስዎ ስላነበቡላቸው ወይም ስለነገሯቸው ተረቶች/ታሪኮች ወይም ርዕሰጉዳዮች ያሏቸውን አስተያየቶች ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው:: ይህም የአንብቦ መረዳትንና በቋንቋቸው ራሳቸውን በአግባቡ የመግለጽ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል::

4. ለልጆችዎ ራስዎ ወይም ሌሎች ተረት/ታሪክ ያንብቡላቸው፤ ይህም የሚያነቡት ጽሑፍ በሌላ ሰው ሲነበብ ምን እንደሚመስል ለልጆቹ የማዳመጥ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፤ በራሳቸውም ለማንበብም ፍላጎት ያሳድርባቸዋል:: ከልጆቹም ጋር ስላነበባችሁት ጽሑፍ ተወያዩ::

5. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ለደረጃቸው የሚመጥኑ ቀላል ጽሑፎችን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው:: ለማንበብ የሚቸገሩባቸውን ቃላትና ዓርፍተነገሮች እንዲያነቡ ያግዟቸው::

6. ልጆችዎ በራሳቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው::

7. ልጆችዎ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ለምሳሌ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞቻቸው ደብዳቤ ወይም በዕለቱ ስለተፈጸመ አንድ ነገር ማስታወሻ በመጻፍ ስሜታቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው::

# የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## የትምህርቱ ክፍሎች (ይዘቶች)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱ ትምህርት በምልክት የተጠቆሙ ክፍሎች አሉት፡፡ ጥቂት ክፍሎች በተወሰኑ ትምህርቶች ውስጥ ብቻ የሚከሰቱ ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ክፍሎች ግን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ይገኛሉ፡

# የማዳመጥ ምንባብ

ይህ ክፍል የሚያተኩረው በአዳምጦ መረዳት ላይ ነው፡፡

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- በመምህራቸው የሚነበበውን ተረት/ታሪክ ወይም መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ያዳምጣሉ፤
- ርዕሱንና ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ/ያስባሉ፤
- ስላዳመጡት ምንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በቃላቸው ወይም በጽሑፍ ስለምንባቡ ያላቸውን አስተያየት ለሌሎች ያጋራሉ፡፡

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ስለምንባቡ የሚያስታውሱትን እንዲነግሯችሁ ይጠይቁ፡፡
- የሚያስታውሷቸውን በጣም ተፈላጊ ቃላት ወይም ስለምንባቡ ያላቸውን ሀሳብ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ተረቱን/ታሪኩን እንዲያሳጥሩ ወይም መልሰው እንዲተርቱ/እንዲተርኩ ይጠይቁ፡፡

# ማጣመር/መነጠል

ይህ ክፍል ቃላትን በማንበብና ወደተለያዩ አሀዶች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያግዛቸዋል፡፡ በ4ኛ ክፍል ደረጃ ልጆች ፍቺ ባላቸው የቃላት አሀዶች (ምዕላዶች) ላይ የበለጠ ያተኩራሉ፡፡

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፣

- ቃላትን “ማጣመር”:- ቃላቱ የተመሠረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሀዶች ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይሷቸዋል::
- ቃላትን “መነጠል”:- ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደአነስተኛ አሀዶች ይነጥላሉ::
- ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሀዶች (ቅጥያዎች) ይለያሉ፤ ያነባሉ፤ ይረዳሉ::

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎን ቃላትን በተለይም በጽሑፉ/ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙትን ረጃጅም ቃላት እንዴት እንደሚያጣምሩና እንደሚነጥሉ ይጠይቋቸው:: ይሄ ለልጆቹ ጠቃሚ ልምምድ ነው::

## ግለንባብ

ይህ ክፍል ዓረፍተነገሮችን፣ አጫጭር ተረቶችን/ታሪኮችን ወይም መረጃ ሰጪ ምንባቦችን በማንበብ ላይ ያተኩራል:: ከዚህ በተጨማሪም በአንብቦ መረዳትም ላይ ያተኩራል::

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ:-

- ግለንባቡን ያነባሉ፤
- ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በግለንባቡ ላይ ይወያያሉ፤
- ስለምንባቡ በደረጃቸው ይጽፋሉ::

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- የዕለቱን ግለንባብ ይመልከቱና ልጆቹ እንዲያነቡ ይጠይቋቸው::
- የቀደሙ ግለንባቦችን ይመልከቱና እንዲያነቡ ይጠይቋቸው::
- ልጆችዎ በግለንባቡ ውስጥ ለማንበብ የሚቸገሩባቸው ማናቸውም ቃላት ካሉ ቃላቱን እንዲለዩዋቸውና ዓረፍተነገሩን መልሰው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው::
- ልጆችዎ ስለግለንባቡ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ይጠይቋቸው::

## ቃላት

ይህ ክፍል አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም እንዲሁም የቃላቱን ፍቺ ከዐውድ ፈልጎ በማግኘት ስልት (ዘዴ) ላይ ያተኩራል።

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፣

- ከመምህራቸውና ከሚያዳምጡት ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ።
- አዳዲስ ቃላትን ከብያኔዎቻቸው ወይም ከሌሎች ቃላት ጋር ያዛምዳሉ።
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ።
- ቃላቱን በዓረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።
- በዓረፍተነገር ወይም በጽሑፍ ውስጥ ባላቸው ዐውድ መሠረት የቃላትን ፍቺ ለመወሰን ጥረት ያደርጋሉ።

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ ስለተማሯቸው ቃላት እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።

## መጻፍ

ይህ ክፍል ቃላትን፣ ዓረፍተነገሮችንና አንቀጾችን በመጻፍ ላይ ያተኩራል።

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ቃላትን መጻፍና በሥርዓቱ መሠረት የቃላቱን ፊደሎች መሰደር ይለማመዳሉ፤
- አጫጭር የቃል ጽሕፈትና የፊደል አሰዳደር ሙከራዎች ይወስዳሉ፤
- ሀሳባቸውን ለሌሎች ለማጋራት ዓረፍተነገሮችንና አጫጭር አንቀጾችን ይጽፋሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ የእጅ ጽሕፈታቸውን እንዲያሻሽሉ ፊደሎችንና ቃላትን እንዲገለብጡ ይጠይቋቸው፡፡
- ቃላትን በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያለማምዱ፡፡
- ልጆችዎ በሚሳሳቱበት ጊዜ ያበረታቷቸው፡፡
- በተጨማሪም ልጆችዎ ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት አጫጭር ታሪኮችን/አንቀጾችን በመጻፍ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

# 1ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ታታሪዎቹ ልጆች



በአንድ አካባቢ አስቴርና ሄኖክ የሚባሉ ጓደኛሞች ነበሩ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። የሚኖሩበት አካባቢ ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ነበር። በአካባቢው የነዋሪዎች ቁጥር በመጨመሩ ጫካው ለእርሻ ሥራ ቀስ በቀስ ተመነጠረ፤ ተጨፈጨፈ።

በዚህም ምክንያት በአካባቢው ሙቀትና ድርቅ ተስፋፋ። አንድ ቀን ሄኖክና አስቴር በድንገት መስቀለኛ መንገድ ላይ ተገናኙ። አስቴር ከፊቷ ላይ ላብ ጠብ ጠብ ይላል። “ሄኖክ እንዴት ነህ?” አለችው። ሄኖክም፣ “ደህና ነኝ፤ አንቺ እንዴት ነሽ?” አላት። “ሙቀት እኮ አቀለጠን!” አለችው። “ልክ ነሽ” አላት። “ሙቀቱን የምንቀይርበት መላ ይኖር ይሆን?” አለችው። “አይጠፋም፤ እስኪ ባለሙያ እናማክራለን” አላት። ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ።

በማግስቱ ተገናኙ። ተያይዘው ወደአካባቢው የደን ልማት ቢሮ ሄዱ። ከቢሮው እንደደረሱ ጉዳዩ የሚመለከተውን ባለሙያ አገኙ። ወደቢሮው ገቡ። “እርስዎን ፈልገን ነበር” አሏቸው። “ለምን ጉዳይ ነው?” አሏቸው። አስቴር ቀደም ብላ፣ “የአካባቢያችን ሙቀት በመጨመሩ፣ መፍትሔ ፍለጋ ነው የመጣነው” አለቻቸው። አቶ አወቀም “መልካም፣ የሙቀት መጠን መጨመር የዓለምም ችግር እየሆነ መጥቷል፤ ለዚህ አሳሳቢ ችግር አንደኛው ምክንያት የአደጉት አገሮች በካይ መርዛማ

ጭስ ወደህዋ መልቀቃቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ የደን መጨፍጨፍ ነው፤ ለዚህም መፍትሔው፣ ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ መጠቀምና ደን ማልማት ነው" አሏቸው።

በሚቀጥለው ቀን ተገናኝተው የአካባቢያቸውን ነዋሪ ለስብሰባ ጠሩ። የአካባቢያቸውን የሙቀት መጨመር መፍትሔ በሚመለከት አወያዩ። ህዝቡን አሳመኑ። ደን ማልማትና መንከባከብ እንዳለባቸው ተስማሙ። ከግብርና ጽ/ቤት ችግኞች እንዲሰጣቸው ጠይቀው ተሰጣቸው። ችግኞቹን በተራቆተው አካባቢ ተከሏቸው። ችግኞቹን ያለመሰልቸት ተንከባከቡ፤ ጠበቁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማየት ቻሉ፤ በተገኘው ውጤት የአካባቢው ህዝብና እነአስቴር ተደሰቱ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

የአየር ንብረት

### ቃላት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

ሀ. ውርጭ　　ለ. ቅዝቃዜ　　ሐ. ነፋሻ　　መ. ብርድ

### መነጠል

የባለቤትነት አመልካች ቅጥያዎችን በምሳሌው መሠረት ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ቤቱ = ቤት - ኡ　　2. ቤቷ = ቤት - ዋ

ሀ. መጽሐፉ　　ሐ. አሻንጉሊቷ　　ሠ. ደረቱ

ለ. ቦርሳው　　መ. ችግኙ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

የሚከተለውን ጥያቄ በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

የጽሑፉ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. የአየር ንብረት　　ለ. መላ　　ሐ. ህዋ

### መጻፍ

የተራቆተ መሬት መልሶ እንዲያገግም ምን መደረግ እንዳለበት ተገቢ ስርዓተነጥብ በመጠቀም ስድስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የአየር ንብረት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ጻፉ።

ሀ. በምንባቡ የተገለጹት የአየር ንብረቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ውርጭ በብዛት የሚታይባቸው አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው?

ሐ. ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ መልእክት በሦስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ስሩ።

ሀ. ከፍተኛ ለ. ተመቻቸ ሐ. ተስማሚ መ. አዝርእት

### መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ።

ሀ. በጉ ለ. ጠረጴዛው ሐ. ወፉ መ. ተማሪው

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተለውን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

ታታሪነት በምን ይገለጻል?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. “መስቀለኛ መንገድ” ምን ማለት ነው?

ለ. ባለታሪኮቹ የሚኖሩት የት ነበር?

### ቃላት

የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. መላ ለ. መፍትሔ ሐ. ማሳመን መ. ፈነደቀ ሠ. በካይ

## መጻፍ

ካነበባችሁት ምንባብ የተገነዘባችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ተገቢ ስርዓተነጥብ በመጠቀም በራሳችሁ አባባል በአራት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

## ግለንባብ

# ሳይቃጠል በቅጠል

ደኖች ለሰው ልጅ በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ፡፡ የአካባቢን የአየር ንብረት ይጠብቃሉ፤ ለዝናብ መዝነብ ምክንያት ይሆናሉ፤ የከርሰ ምድር ውሃን ጠብቀው ያቆያሉ፤ የአፈር መሸርሸርን ይከላከላሉ፤ የቅጠላቸው ብስባሽ ለማዳበሪያነት አገልግሎት ይውላል፡፡ የፀሐይን ሙቀት ይከላከላሉ፡፡

ይሁን እንጂ፣ ጠቀሜታቸውን በውል ባልተገነዘቡና ኃላፊነት በማይሰማቸው ግለሰቦች ደኖች ይጨፈጨፋሉ፤ ይቃጠላሉ፤ ይመነጠራሉ፡፡ ህግ ሳይፈቅድላቸው በራሳቸው ፍላጎት ህገወጥ ሰፈራ ያካሂዳሉ፡፡ የመነጠሩትን መሬት ቁልቁል በማረስ ለም አፈሩ በጎርፍ ታጥቦ እንዲሄድ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ አሉታዊ ተግባራት ለምግብ እህል ምርት መቀነስ ሰበብ ሲሆኑ መሬቱ ከነአካቴው እህል እንዳይበቅልበት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ሰውሠራሽ ጎጂ ተግባራት አካባቢን ወደበርሃማነት ይቀይራሉ፡፡ የምግብ እህል እጥረትን፣ ሞትንና ስደትንም ያስከትላሉ፡፡

ከብቶችን በደኖች አካባቢ ለግጦሽ ማሰማራትም ሌላው ችግር ነው፡፡ ከብቶች በደኖች አካባቢ ሲሰማሩ ለጋ ተክሎችን ይሰባብራሉ፤ የዛፎችን ቅጠሎች ያራግፋሉ፡፡ በዚህ የተነሳ የደን ሃብት ይመናመናል፡፡ የደን ሃብት መመናመን ደግሞ ለዱር እንስሳት መሰደድ ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለዚህ “ሳይቃጠል በቅጠል” እንደሚባለው ድርጊቱን ከወዲሁ ማስቆም የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**አረንጓዴው ዘመቻ**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ደኖች ሲቃጠሉና ሲመነጠሩ የሚጎዱት እነማን ናቸው?

ለ. ደን አገገመ የምንለው ምን ዓይነት ለውጥ ሲያሳይ ነው?

### ቃላት

**ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቺ በቃላችሁ ስጡ፡፡**

ሀ. አሳሳቢ ለ. ተሣታፊ ሐ. በነቂስ መ. ገጠማቸው

### መነጠል

**በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ. ሜዳዎች ለ. ችግሮች ሐ. ክፉዎች መ. ጎበዞች

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ህገወጥ ሰፈራ ምን ያስከትላል?

ለ. አካባቢን ከጎጂ ልማዳዊ ተግባራት ነጻ ማድረግ ምን ጠቀሜታ አለው?

ሐ. ከብቶችን በደኖች አካባቢ ለግጦሽ ማሰማራት ምን ችግር ያመጣል?

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::

   ሀ. ጠቀሜታ ለ. ሰፈራ ሐ. መጠበቅ

2. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት የሚያስተላልፉትን መልእክት በቃል ግለጹ::

   ሀ. ደን ጭፍጨፋ ለ. ቃጠሎ ሐ. ህገወጥ ሰፈራ መ. መሰደድ

## መጻፍ

"የደን ጥቅም" በሚል ርእስ ተገቢ ስርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀፅ ጻፉ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### አረንጓዴው ዘመቻ

## ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. ባለሙያ ለ. ማሠማራት ሐ. መከለል መ. ማጠቃለል

2. ለጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. የተመናመነን ደን ወደ ቀድሞው ለመመለስ መከናወን ያለባቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው?

   ለ. የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድን ነው?

## መነጠልና ማጣመር

1. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ::

   ሀ. ገበሬዎች ለ. በረሃዎች ሐ. ሰነፎች መ. ጠይሞች

2. ዋናውን ቃልና ቅጥያውን አጣምራችሁ ፃፉ::

ሀ. ድመት-ኦች ለ. ከተማ-ዎች ሐ. ረባሽ-ኦች ሐ. አሞራ-ዎች